

# IRS የአዘርባጃን ቅርስ



የሺኪካውካሰስ ቤተመንግስት ጌጥ በ18ኛው ክፍለ ዘመን



ሉብኡ ኣኽመዶቭ

# የአዘርባጃን የኪነ ህንፃ ጥበብ ቅርስ

# የአዘርባጃን ቅርስ



የተፈጥሮ መስህብ ባለው ተዳፋት የታላቁ በታሪኳ ከተማዋ ሁለት ስሞች ነበሯት- ሼኪና ኑካ፡ ፡ “ሼኪ” የሚለው ቃል በዚህ ክልል ከኖረው ጥንታዊ የቱርኪክ ሳካ ጎሳ የመጣ ነው፡፡ በዘመናት ሂደት በአዘርባጃኒ ቋንቋ የሥነ ድምጽ ሕግ መሠረት ቃሉ ወደ ሻካ- ሻኪ- ሼኪ ተለውጧል፡፡ የቱርኪክ ጎሣ ለረጅም ጊዜ እዚህ ሥፍራ መኖር የቻለው በመቶዎች በሚቆጠሩ ጥንታዊ የመቃብር ክምር ሲሆን የኪነ ሕንጻ ጥናቱ በንጽጽር በቅርብ ጊዜ ነበር የተጀመረው፡፡




በዚሁ ጊዜ በጥንተ ታሪክ ድርሳናት “ናኪያ” የሚለው ሥም ተጠቅሷል፡፡ ሼኪ እና ናኪያ በኪሽ ወንዝ ዳርቻ የሚገኙ ሁለት ጥንታዊ የመኖሪያ ቦታዎች መሆናቸውን ተመራማሪዎች አረጋግጠዋል፡፡ ናኪያ- ኑካ የመኖሪያ አካባቢ ከነበረ በንግድ መስመር አቅራቢያ የምትገኘው ሼኪ በፍጥነት አድጋለች ማለት ይቻላል፡፡ ሆኖም በ1772 በአካባቢው በዘነበው ከባድ ዝናብ ምክንያት የኪርሽ ወንዝ ሞልቶ አካባቢውን በማጥለቅለቁ ሼኪ ሙሉ በሙሉ ወደመች፡፡ ካቭካዝ ጋዜጣ (15 ጁላይ 1846) እንደዘገበው “...... የዚህ መጥፎ የጎርፍ መጥለቅለቅ አደጋ መንስኤው ሼኪን ወደ ፍርሽራሽ የቀየረውና ቤቶቿን ጠራርጎ የወሰደው የሼኪ ወንዝ ሙላት ነው....፡፡ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች የዚህ የአስከፊ የጎርፍ መጥለቅለቅ አደጋ ሰለባ ሆነዋል... ከዚያም የሼኪ ነዋሪዎች- በተራራው ግርጌ ወደሚገኘው- የሸለቆው ምሥራቃዊ የወንዝ ዳርቻ ተዛወሩ፡፡ እዚህ ሥፍራ የዛሬዋን ኑካ ከተማ ቆረቆሩ”፡

፡ ከጎርፍ መጥለቅለቁ በኋላ ሕዝቡ ወደ ኑካ መንደር ተዛወረ፣ ከተማዋም ኑካ በሚል ስም መጠራት ጀመረች፡፡ ቀደም ሲል በ19ኛው ክፍለ ዘመን ከተማዋ በከፍተኛ ደረጃ ከመስፋፋቷ የተነሳ የቀድሞውን የሼኪ ጠረፍና ኑካን ራሱን የሸፈነች ቢሆንም ይህ ስም እስከ 1968 ህጋዊ ሆኖ ቆይቷል፡፡

እንደ ሕዝብ መኖሪያ ማዕከል ሼኪ ከተቆረቆረች ከ2,500 አመት በላይ እንደሚሆናት የአርኪዎሎጂ ቁፋሮ ጥናቶች ያሳያሉ፤ ይህም የካውካሰስ ጥንታዊ የመኖሪያ ሥፍራዎች አንዷ ያደርጋታል ማለት ነው፡፡ በአንደኛው ክፍለ ዘመን ከተማዋ የካውካሺያን አልባኒያ አካል ነበረች፡፡ በከተማዋ አቅራቢያ በአልባኒያ ወታደሮችና በፖምፔ በተመራው የሮማን ወራሪ ኃይል መካከል የሚካሄድ ጦርነት ነበር፡ ፡ የአልባኒያ ነገሥታት ክርስትናን በተቀበሉበት ጊዜ በሼኪ ግዛት በርካታ አብያተ ክርስቲያናት ተሠሩ፣ ምክንያቱም ከዚህ ሥፍራ ክርስትናን ወደ ሰሜን፣ ወደ ካውካሰስ ተራራማ ቦታዎች ለማስፋፋት በማሰባቸው ነበር፡፡ በ7ኛውና በ8ኛው ክፍለ ዘመን ከተማዋ በአረብ ኃይሎች ከዚያም በአረብ-ካዛን ጦርነት ዘመቻዎች ምክንያት ከባድ ጉዳት ደረሰባት፡፡ ከ9ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ከተማዋ የአዘርባጃን ሻዳዲድ ከዚያም የኤልደኒዚድ ስቴት አካል ነበረች፡፡ ከሞንጎሊ ወረራዎች በኋላ ከተማዋ ማንሰራራት ጀመረች፣ እዚያ በ14ኛው ክፍለ ዘመን ነጻ የሺኪ ይዞታ ተመሠረተ፡፡ ሼኪ ለ14 አመታት የኤሚር ቲሙን ሠራዊት ለመቋቋም ለተዋጉት የአሊንጃ-ጋላ የመከላከያ ኃይሎች ምሽግ ለማጠናከር ከፍተኛ እገዛ አድርጋለች፡፡ የሼኪ ገዥ የኦሪያት ሥርወ መንግሥት ሰይድ አሊ በአሊንጃ- ጋላ ግንብ ሞተ፣ ይህም የአዘርባጃን ሕዝብ የጀግንነትና አገርን የመከላከል ተምሳሌት ለመሆን በቅቷል፡ ፡ በ1396 ቲሙሪዶች ከተማዋን ቢያወድሙም የሟቹ ገዥ ልጅ ሰይድ አሕመድ ከተማዋን መልሶ ማቋቋም ችሏል፡ ፡ ከ15ኛው ክፍለ ዘመን ይቺ የአዘርባጃ ከተማ በምርጥ ሃር ምርት የምትታወቅ ለመሆን በቅታለች፡፡ በጋራ-ኬሺሽ ኦግሉ ሥርወ መንግሥት (ከ1444-1551 ሼኪ ነጻነቷን ጠብቃለች፡፡ በ1551 ብቻ ነበር ቀዳማዊ ሳፋቪድ ሻህ ታህማሲብ ከተማዋን ይዞ ወደ ሳፋቪድ ስቴት ያጠቃለላት፡፡

በ17ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ሼኪ በናድር ሻህ አፍሻ ላይ በተከታታይ የተፈጸሙ አመጾች አስተናግዳለች፡፡ ሻህ የሚያራምደው ፖሊሲ የኢኮኖሚ ውድመትና ማንኛውም ተቃውሞ በኃይል መጨፍለቅ አስከትሏል፡፡

በ1743 የአካባቢው የፊውዳል ባላባት ሃጂ ቻላቢ (ከ1743-1755) አመጽ አስነስቶ የሻህ አገዛዝ ለመቀበል አሻፈረኝ አለ፡ ፡ ናዲር ሻህ ከፍተኛ ብዛት ያለው ጦር አሰማርቶ በአራት ወር ጥቃት የአማጺዎችን ይዞታ በ1744 የጋላርሳን-ጎራሳን ግንብን ተቆጣጠረ (መጥታችሁ እዩ)፡፡ በናድር ትዕዛዝ ከተማዋ ተደመሰሰች መስኮችና የአትክልት ቦታዎችም ወደሙ፡ ፡ ሆኖም ይሄ ሁሉ ጥቃት የሻኪን ነዋሪዎችን ልብ መስበር አልቻለም፡፡ ናድር ሻህ ያወደማቸውን ምሽጎች ትቶ ሼኪን ለመልቀቅ ተገደደ፡፡ በዚህ ምክንያት ነጻ ሼኪ ተመሠረተች፡



፡ ከ1772 የጎርፍ መጥለቅለቅ በኋላ ከተማዋ እንደ አዲስ ተገነባች፣ ምሽጎች፣ የቤተመንግሥት ሕንጻዎች፣ መስጊዶች፣ የሲራራ ነጋዴዎች መጠለያዎችም ተሠሩ፡፡ በ1805 ከተማዋ የሩስያ ኢምፓየር አካል ሆነች፣ የቻላቢ ሥርወ መንግሥት ሥልጣኑን አጣ፣ በ1819 የሼኪ ካናቴ ተወግዶ የኑካ ካውንቲ ተመሠረተ፡፡

በሶቪየት ዘመን ከተማዋ ዋና የግብርናና የኢንዱስትሪ ማዕከል ሆነች፡፡ የሃር ምርት አምራቾች ማህበር፣ የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ፣ የትምባሆ-ማብላያ፣ የብሎኬት ፋብሪካዎች፣ የሥጋ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ የምግብ ፋብሪካዎች እንዲሁም የተለያዩ የትምህርትና የባህል ተቋማት በከተማዋ ተቋቁመዋል፡፡

ዛሬ ሼኪ የዳበረ መሠረተ ልማት ያላት የአዘርባጃን ውብ ከተማና ከአገሪቱ የባህል ቱሪዝም ዋና ዋና መዳረሻ ከተሞች አንዷ ናት፡፡

ከጥንታዊ የአዘርባጃን ከተሞች አንዷ የሆነችው ሼኪ በትክክል የአገሪቱ የኪነ ሕንጻ ቅርስ ማዕከል በሚል መጠሪያ ትታወቃለች፡፡ በርካታ የጥንታዊና የመካከለኛው ዘመን ሃውልቶችና የ18ኛውና የ19ኛው ክፍለ ዘመን ሃውልቶች አሏት፡፡ የታሪካዊቷ ከተማ የላይኛው ክፍል ዩካሃሪ ባሽ በሚል



መጠሪያ ይታወቃል፣ የስቴቱ ታሪካዊ የኪነ ሕንጻ ቅርስ ተብሎ ታውጇል፡፡ ይህ ምሽግ፣ የሼኪ ካንስ ቤተመንግሥትንና የተለያዩ የመንግሥትና የኃይማኖት ተቋማት ሕንጻዎችን ይጨምራል፡፡

የሼኪ ምሽግ በተሻለ ደረጃ ጥበቃ ከሚደረግላቸው የመከላከያ ኪነ ሕንጻ መዋቅሮች አንዱ ነው፡፡ እዚህ የግንቡ ጠቅላላ ርዝመት 1.3 ሚሎ ሜትር፣ ከፍታው 4.8 ሜትር ሆኖ ሁለት በሮችና 21 ማማዎች አሉት፡፡

የሼኪ ካሃንስ ቤተመንግሥት አለማቀፋዊ ፋይዳ ያለው የታሪካዊና የባህላዊ ሃውልት ቅርስ ነው፡፡ ከ18ኛው ክፍለ ዘመን የካውካሰስ ምርጥ የቤተመንግሥት ኪነሕንጻዎች ናሙናዎችና ከእስላማዊ ምሥራቅ እንቁዎች አንዱ ነው፡፡ ገንቢዎቹ የተወሰኑ የርእደ መሬት መከላከያ ቀበቶዎችን ተጠቅመዋል፣ ቤተመንግሥቱ ከባድ የመሬት መንቀጥቀጥ አደጋዎች ሊያስከትሉ የሚችሉትን ጉዳት ተቋቁሟል፡፡ የቤተ መንግሥቱ የፊት ገጽ ውስጡም (በጠቅላላው 300 ካሜ ስፋት ያለው) አደንና ጦርነትን የሚያሳዩ ቅብ ሥዕሎች እንዲሁም የጂኦሜትሪና የአበባ ንድፎች ያሉት ነው፡፡ በመሃሉ ግዙፍ የቀለማት ህብር የመስኮት መስታወት ሥዕል አለው፡፡ በተጨማሪም የፊት መስታወት ባልኮኒ አለ፡፡ የቤተመንግሥቱ መስኮቶች በሻባካ ቴክኖሎጂ ምስማርና ማጣበቂያ በሌለባቸው የከለር ቬኔሽያን መስታወቶች የተሠሩ ናቸው፡፡ አንድ ካሬ ሜትር የቀለም መስታወት በ3.7 ሺ ቁርጥራጮች ነው የተሠራው፣ በዚህም ምክንያት ነው አንድ ባለቀለም የመስኮት መስታወት ለመሥራት ከ5-6 ወር የፈጀው፡፡ በደርዘኖች የሚቆጠሩ የሩሲያና የአውሮጳ ተጓዦችና ተመራማሪዎች በተለያየ መንገድ ቤተመንግሥቱን ገልጸውታል፡፡ ጄኔራል ኒኮላይ ራይቭስኪ ሲጽፍ "....በዚህ አካባቢ የቀድሞው የከሃን ቤተመንግሥት በጣም ውብ ነው፣ የባክቼሳሪ ቤተመንግሥት ግን ስለዚህ ብዙ ፍንጭ አይሰጥም..." ይላል፡፡ በ1858 ሼኪን የጎበኘው ደራሲ ሰር አሌክሳንደር ዱማስ ሲጽፍ "የካን ቤተመንግሥት ማራኪ ሕንጻ ነው፡፡ የሕንጻውን አስደናቂ ገጥታ ብሩስ ብቻ ነው መግለጽ የሚችለው....ይህን የኑካ ማራኪ ቤተመንግሥት እግዚአብሄር ከአጥፊዎች ይጠብቅልን" ብሏል፡፡ በሺዎች የሚቆጠሩ ቱሪስቶች ቤተመንግሥቱን ይጎበኛሉ፤ በዚህ ልዩ አገልግሎት የቅርጽ ብልጽግናና የቀለማት ቅርጾች ይደመማሉ፡፡

በንግድ በምትታወቀው ሼኪ በርካታ የገበያ ቦታዎች (ኢስፋን፣ ታብሪዝ፣ ሌዝጊን፣ ወዘተ) ነበሩ፣ ትልልቆቹ የላይኛውና የታችኛው የገበያ ቦታዎች በ18ኛው ክፍለ ዘመን ነበር የተሰሩት፡፡

የላይኛው የገበያ ቦታ 242 ክፍሎች ያሉት ሲሆን የታችኛው 200 ክፍሎች ነበሩት፡፡ መጋዘኖች የችርቻሮ መደብሮችና የእንስሳት በረቶችም ነበሯቸው፡፡ ዛሬ እነዚህ የገበያ ቦታዎች ታድሰው የተለያዩ የባህል ሁነቶችንና ፌስቲቫሎችን ያስተናግዳሉ፡፡ ከእነዚህ አንዱ የሼኪ ካራቫንሰሪ ሆቴል ይገኝበታል፡፡ ከተማዋ (የቆሻሻ ውሃ ማስወገጃ) ቦዮችና ከሴራሚክ ቱቦ የተሠሩ የመካከለኛው ዘመን የፍሳሽ መስመሮች አሏት፣ በዚህ ምክንያት ከተማዋ ከጽዳት አንጻር ከሙስሊም ምሥራቅ ጽዱ ከተሞች አንዷ ተደርጋ ትቆጠራለች፡፡ በሼኪ አቅራቢያ በኪሽ መንደር እስካሁን የአልባኒያ ቤተክርስቲያን ይገኛል፡፡ አመሠራረቱ ከክርስቲያኑ ቅዱስ ኤሊሻ ሥም የተያያዘ ነው፡፡ ቤተክርስቲያኑ በአዘርባጃንና በኖርዌ ሳይንቲስቶች ተጠንቶ ታድሷል፡፡ በመስኩ የተደረገው ትንተና የሃይማኖት መዋቅሩ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ3000 አመተ አለም እንደተሠራ፣ ሆኖም የተረፈው ሕንጻ ከዚያ ወዲህ እንደተሠራ ያሳያል፡፡ የበርካታ የአዘርባጃን ታሪካዊ ሃውልቶችን እድሳት ያከናወነው የታዋቂው የኖርዌ አሳሽ የቶር ሃይደርዳሂ የአንገት በላይ ቅርጽ ሃውልት በመቅደሱ አጠገብ ቆሟል፡፡ በጋራታፓ ተራራ አናት ከ14ኛው እስከ 18ኛው ክፍለ ዘመን የነበረውን ደም አፋሳሽ ሁነት የሚያሳይ የመካከለኛው ዘመን የጋላርሳን-ጎራሳን ምሽግ ይገኛል፡፡ የካን መስጊድ፣ የኦማር አፈንዲ መስጊድና የጊሌይሊ ሚናሬት የእስላማዊ ኪነ ሕንጻ ልዩ ምሣሌዎች ናቸው፡፡ የኦርታ ዘይት መንደር ማማና ቤተክርስቲያን፣ የባርባራትማ መንደር ማውሶሎኒየም፣ የአይዲን-ቡላግ መንደር ማማ፣ የሼክሃኖቮስ ቤቶችና የመካከለኛው ዘመን ገላ መታጠቢያ ቤቶች ከሼኪ ታሪካዊና ባህላዊ ሃውልቶች ከብዙ



በጥቂቱ ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው፡፡

በሼኪ ግዛት በርካታ የተፈጥሮ ሃውልቶችም አሉ፡፡ በመሆኑም ሁለቱ ልዩ ዛፎች- የካን ቺናርስ (ሲናሞርስ) ከ500 አመት በላይ እድሜ ያለው ሲሆን የቱሪስት መስህብም ነው፡፡ የዛፉ ክብ 11.5 ስፋት ያለው ሲሆን ቁመቱ 33.34 ሜትር ነው፡፡

የከተማዋ ክፍሎች ጥንታዊ ታሪካዊ ስሞች አሏቸው፡- እነዚህም አግቫኒር (አግቫንስ)፣ ዱሉዝቹላር (ሸክላ ሰሪዎች)፣ ዛርጋርላር (የወርቅና ብር ጌጣጌጥ ሠሪዎች)፣ ሃልቫቺላር (ጣፋጭ ምግቦች አዘጋጆች)፣ ይጨምራሉ፤ ብዙዎቹ የእደ ጥበባትን ብዝሃነት የሚያሳዩ ሲሆን አንዳንዶቹ ስሞች እስካሁን ይሰራባቸዋል፡፡



በመልማት ላይ ከሚገኙት የእደ ጥበባት ዘርፎች አንዱ ወደ ትክክለኛ ኢንዱስትሪ ደረጃ ተሸጋግሯል፡፡ ይህም የሃር ምርትና የሃር ውጤቶች ማምረቻ ኢንዱስትሪ ነው፡፡ ሼኪ በታላቁ የሃር መንገድ መተላለፊያ ላይ የምትገኝ ሲሆን ለብዙ ክፍለ ዘመናት የሲራራ ነጋዴዎች መደረሻ ነበረች፡፡ ከዚህ ሥፍራ ምርጥ የሃር ጨርቃ ጨርቅና የወርቅ ጥልፍ የሻዋል ምርቶች ወደውጪ የሚልኩ ነጋዴዎችና ተጓዦች ነበሩ፡፡ የሼኪ የሃር ምርት ከ15ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ታዋቂ ስስ፣ ብርሃን የሚያስተላልፍ ጠንካራና ከቻይና ሃር በዋጋ ርካሽ ምርት ነው፡፡ እዚህ ለራሳቸው የብርድ ልብስ፣ የሻዋልና የ“ካላጋይስ” ሸመና ውጤቶች ያመርቱ ነበር፡፡ ከ16ኛው ክፍለ

# የአዘርባጃን ቅርስ





ዘመን ወዲህ ሼኪ የካውካሰስ የሃር ምርት ማዕከል ለመሆን በቅታለች፡፡ የመጀመሪያው የሃር ማምረቻ - በአዘርበጃን የመጀመሪያው ማምረቻ- በ1829 በሼኪ ተመሠረተ፡፡ በ1861 የመጀመሪያው የሃር ጨርቅ ማምረቻ - በአለም ትልልቆቹ አንዱ- እዚህ ተቋቋመ፡፡ በ19ኛውና በ20ኛው ክልለ ዘመን መጀመሪያ ከተማዋ የፈረንሳይ የሃር ምርት ማዕከል የሆነችውን የሊዮን ከተማ ምሣሌ በመከተል የካውካስያን ሊዮን በሚል መጠሪያም ትታወቅ ነበር፡፡

ከ1931 ጀምሮ የተፈጥሮ ማቅለሚያዎችን በመጠቀም ሣዋልና ስካርፍ የሚያመርተው የሃር ፋብሪካ አሁንም የሃር ምንጣፍ በማምረት ላይ ይገኛል፡፡

የሼኪ የማይዳሰስ የባህል ቅርስም ልዩ ነው፡፡ የመጀመሪያው የሼኪ ቀበልኛ የአዘርባጃን ቋንቋ ዘይቤ ነው፡ ፡ ሁለተኛው የሼኪ ነዋሪዎች የጨዋታ ለዛና ቀልድ የማውራት ችሎታ ነው፡፡ ሼኪ በቀልድ የምትታወቀው የቡልጋሪያ ጋብሮቮ ከተማ እህት ከተማ የሆነችው በአጋጣሚ አይደለም፡ ፡ በበጋና በክረምት በሜዳ ላይ የሳቅ ቲያትር በሼኪ ይታያል፡፡ በመጨረሻም ሼኪ በምግብ ዝግጅት ታዋቂ ነች፡፡

የሼኪ ሃቫ፣ የሼኪ ፒቲ (በልዩ የሸክላ ድስት የሚሠራ የአትክልት ወጥ) ባልቫ፣ ሼኪ፣ ጉርዛ፣ ባሚያ፣ ፔሸቬንክ፣ ጊርማዳም፣ ሼኪ ኩልቻ፣ ቴል፣ ሼኪ ኦቨማ የሼኪ የምግብ ዝግጅት ወጥቤቶች ድንቅ ሥራዎች ማሳያ ናሙናዎች፣



የእነዚህ ሚስጥር እስካሁን ድረስ አልጠፋም፡፡ በባህላዊ የምግብ አዘገጃጀት መሠረት የሚጋገሩ የምሥራቅ ጣፋጭ ምግቦች ከትውልድ ወደትውልድ እየተላለፉ የመጡ ናቸው፡፡ ከተራራ እጽዋት የሚገኙ ዋልነት፣ ሄዜልነት፣ ለውዝ፣ ማር ልዩ ልዩ ማጣፈጫ ጣዕም ያስገኛሉ፡፡ በሼኪ የጣፋጭ ምግቦች አዘጋጅ ልዩ ሙያ ያለው ባለሙያ ነው፡፡

በደን በተሸፈኑ ተራሮች መካከል የምትገኘው ሼኪ በጣም ነፋሻ የአየር ንብረት አላት፡፡ በአካባቢው ያሉት የተራራ ደኖች ከተማዋን ከልክ ካለፈ ሙቀት ይከላከላሉ፣ ከተማዋን ከጎርፍ ይጠብቃሉ፣ የከተማዋን ዕይታ ያሳምራሉ፡፡ ከተማዋ የበለጸገ የዱር እንስሳት ኃብትም አላት፡፡ ይህ አስደናቂና ውብ የተራራ አካባቢ መስህብ ያላቸው ጥልቅና ጠባብ ሸለቆዎች የሚያቋርጡበት በርካታ ምንጮች፣ ንጹህ ወንዞች፣ ፏፏቴዎች፣ በጥቅጥቅ ደንና በተራራ ሳር ምድር የተከበቡ የማዕድን ምንጮች የሚገኙባቸው፣ በጥንት ጊዜያት በጤነኛ የአየር ንብረት የመዝናኛ ቦታነት የሚታወቁ ናቸው፡፡

ከታሪካዊ- ባህላዊ ቱሪዝም በተጨማሪ የፈረስ (የፈረስ ግልቢያ) ቱሪዝምም በሼኪ ለምቶ ይገኛል፡፡ እዚህ በዳሸዩዝ መንደር በአዘርባጃን የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ሥር



የፈረስ ግልቢያ ቱሪዝም ሪፐብሊካን ማዕከል ይገኛል፡፡ ይህ አእምሯዊና ጤነኛ ቱሪዝም በሚሆን አንድ ወይም ከአንድ ቀን በላይ በሚወስዱ ከሰባት በላይ የጉዞ መስመሮች በሼኪ ወረዳ ወደሚገኙ የተለያዩ አካባቢዎች የሚደረግ ጉዞ ያካትታል፡፡ በዚህ ጊዜ ቱሪስቶች ከክልሉ የበለጸገ የተፈጥሮ ኃብትና ታሪካዊ ቦታዎች ቅርስ ራሳቸውን ማስተዋወቅ ይችላሉ፡፡ ቱሪስቶች በተጨማሪም በቾቫን የፈረስ ጨዋታ (ፖሎ) መሳተፍ ይችላሉ፡፡ ይህ ጨዋታ በቅርቡ በዩኔስኮ የማይዳሰስ







ቅርስ ዝርዝር መዝገብ ተካቷል፡፡

ከሼኪ፣ የጉዞ መስመሮች በአዛርባጃን የተፈጥሮ መስህብ ወዳላቸው ሌሎች የተለያዩ አካባቢዎች ያመራሉ- እነዚህም ከየጋክ፣ የዛጋታላና የባልካን ከተሞችን ይገኙባቸዋል፡፡ ለአካባቢው ነዋሪዎችና ለቱሪስቶች በሚስማማ ሁኔታ የሺን ወንዝ ድልድይ- በአዘርባጃን ረጅሙ ድልድይ (1,300 ሜትር ርዝመት 13 ሜትር ቁመት ያለው) በ2010 በሼኪ ተከፈተ፡፡

ጥንታዊቷ ከተማ ሼኪ የተፈጥሮ ውበትን ማድነቅ የሚፈልጉ፣ ታሪክ የሚወዱና በአካባቢው ልዩ ቀለም መደሰት የሚፈልጉ ጎብኚዎችን ትጠባበቃለች፡፡

ጁላይ 7 ቀን 2019 አዘርባጃን **"ታሪካዊውን የሼኪ ማዕከልና የካሃን ቤተመንግሥት"** በዩኔስኮ **የአለም የቅርስ ዝርዝር** ለማስመዝገብ በእጩነት ያቀረበችው ጥያቄ በባኩ በተካሄደው የዩኔስኮ 43ኛው የአለም ቅርስ ኮሚቴ መደበኛ ስብሰባ በዩኔስኮ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

ሼኪ በአዘርባጃን በካርኮ፣ ፖላንድ በ2007 በተካሄደው የኮሚቴ ስብሰባ በእጩነት ተቀባይነት አግኝታለች፡፡ የአለማቀፍ ሃውልቶችና ሳይቶች አለማቀፍ ምክር ቤት (አይሲኦኤምኦኤስ) ተወካዮች ሪፖርት እንደሚያመለክተው አዘርባጃን የሼኪ ታሪካዊ ማዕከል አካል ለሆኑት የካሃንን ቤተመንግሥትና በአካባቢው ለሚገኙ ጥንታዊ ቦታዎች ጥበቃና መልሶ ግንባታ ጨምሮ ከሁለት አመት በፊት በካርኮው የገባችውን ስምምነት ግዴታ ስትፈጽም ቆይታለች፡፡

የሼኪ ታሪካዊ ማዕከልና የካን ቤተመንግሥት አዘርባጃን በዩኔስኮ በአለም ቅርስነት ካስመዘገበቻቸው ሶስት ሳይቶች ተጨማሪ ነው፡፡ ኢቸሪሼኸር በሚል መጠሪያ የሚታወቀው የባኩ የግንብ ከተማ በየአንጻ በ2000 እና በ2007 በአለም ቅርስነት የተመዘገቡትን የሺሪቫንሻህን ቤተመንግሥትና የመጀመሪያ ማማ፣ የጎቡስታን የአለት ጥበብ ባህላዊ መልክአ ምድር ይጨምራል፡፡

የአዘርባጃን ፕሬዚዳንት ኢልሃም አሊዬቭ እና ተቀዳሚ ምክትል ፕሬዚዳንት መህሪባን አሊዬቫ የሼኪ ታሪካዊ ማዕከል ከካን ቤተመንግስት ጋር በዩኔስኮ የአለም ቅርስ መዝገብ መመዝገቡን ምክንያት በማድረግ ለአዘርባጃን ሕዝብ ባስተላለፉት መልእክት እንኳን ደስ ያላችሁ ብለዋል፡፡